# የፖለቲካ ደንቃሮችና የምሁር ደንቆሮች

ከኃይለ ልዑል ግርማ (ዋሽንግተን ዲሲ)

የሰሞኑ ፖለቲካ ግለትና እንቅስቃሴ ከዛሬ ሶስት ዓመት በፊት ከነበረው እውነተኛ እንቅስቃሴና ግለት ጋር ሲነጻጸር የሰማይና የምድር ርቀት ያህል ይለያያል። "ትግል ድሮ ቀረ" ቢለን አንድ ሰው ብዙ ሲገርመን አይገባም። የሚገርመው የትግሉ አስተባባሪ ነን እያሉ በየቦታው ከተደበቁበት ብቅ ያሉት ሰዎች የቀንጅት መሪዎች በታሰሩበት ጊዜ ትግሉን ነጥቀው አቀጣጫ ያስቀየሩ፣ ለውጭ ኃይልና ለወያኔ በሆዳቸውና በጥቅማቸው የተገዙ ሰዎች ዛሬ "ትግሉን ወደ ነበረበት ቦታ መለስነው" እያሉ ለመፎከር ሲነሱ አለማፈራቸው ለእኛ ይገርማል። ማንነታቸው ተጋልጦ አፍረው ከመድረክ ከጠፉ በኋላ ሰሞኑን ደግሞ ጥቂት በማወቅም ይሁን ባለማወቅ አዳዲስ ሰዎችን ከፊት በማስቀደም "ዓለም አቀፍ ሰላማዊ ሰልፍ" እያሉ ከበሮ ሲመቱና ሲራወጡ ከርመዋል። ወያኔን ለምን ተቃወማችሁ አይደለም አባባሌ እናንተ እነማን ናችሁ? ትላንትና ምን ስታደርጉ ነበር? ዛሬስ መስራት የጀመራችሁትና ከጀርባ የሚያንቀሳቅሷችሁ እነማን ናቸው? የሚለውን ለማንሳት ነው።

ትላንት የሕዝብን ትግል አኮላሽተው፣ ነጥቀው፣ ከድተው የአገር ቤቱንም ሆነ የውጭውን ደጋፊ ልብ ካቆሰሉና በጋለው ትግል ላይ ቀዝቃዛ ውሃ የቸለሱት ሰዎች ዛሬ ደግሞ ለሚቀጥለው ዓመት ምርጫ የተጠነሰሰውን ሴራ ከግብ ለማድረስ የሕዝብን አጀንዳና ትግል ነጥቀው ድራማ ሰርተው መለስን በሌላ መለስ ለመተካት የሚደረግ የረቀቀ ተንኮል ደባ መሆኑን ሕዝብ ሊያውቀው ይገባል።

የሰሞኑን ትግል አስተባባሪ ነን ብለው በየቦታው የተራወጡት የብርቱካን ፓርቲ ደጋፊዎችና የብርሃኑ ነጋ ደጋፊዎች ናቸው። የእነ አንዳርጋቸው ጽጌ የፈጠፈጧቸው የ (KIL)ባለሚሉች ከአጨብጫቢዎቻቸውና ለጥቅማቸው ከተገዙ ሆዳሞች ጋር ከየቦታው ብቅ ብቅ ማለታቸው የዛሬ ድግሳቸው ደግሞ ምንድነው? እንድንል ያስገድደናል። አንድ መታወቅ ያለበት ነገር አለ። የተለያየ ስም ለላቸው የተለያዩ ድርጅቶች ይምሰሉን እንጂ የብርቱካን "አንድነት" ፓርቲና የብርሃኑ ነጋ "ግንቦት ሰባት" አንድም ሁለትም ናቸው። ለምሳሌ አንዲት ማስረጃ ብቻ ብንጠቅስ፣ የአንድነት ፓርቲ ደጋፊዎችና የኮሚቴ አባሎች ናቸው ለግንቦት ሰባት 500 ዶላር እንዲሰበስቡ በየቦታው የተመደቡት ሰዎች። ተመልከቱ የሚሰሩት፣ ዓላማቸው፣ ግባቸው፣ ሴራቸው፣ ደጋፊዎቻቸው ሁሉ አንድ ናቸው። ልዩነታቸው አንዱ አገር ቤት እንቀሳቀሳለሁ ሲል ሌላው በውጭ እንቀሳቀሳለሁ ማለቱ ብቻ ነው። እነዚህ ድርጅቶች ደግሞ በውጭ ያለው ከኦነግና ከኡጋዴን ነጻ አውጭ ጋር ሲሰራ፣ የነብርቱካን ደግሞ ከነሰዬ አብርሃ፣ ከአረና ትግራይ፣ በየነ ጴጥሮስና ወዘተ ጋር መስራታቸው ነው። ግባቸው የ2010 ምርጫ ድራማ መስራትና የመለስን አገዛዝ በሌላ መለስ አገዛዝ ማስቀመጥ ነው። በውጭ ኃይል የተደገሰልን ድግስ ይኼ ነው።

ለመሆኑ እነደዚህ ተጋኖ ብርቱካን ብርቱካን የተባለላትና "ዋና ተቃዋሚ" እየተባለ የሚነገርለት የአንድነት ፓርቲ ስም በአጭር ጊዜ ውስጥ የገነነው ለምንድነው? ብርቱካን ሚዲቅሳ ምን ለሳደረገች ነው ከአጼ ቴዎድሮስ፣ ከእቴጌ ጣይቱ፣ ከበርማዋ ታጋይ እየተነጻጸረች የሚነገርላት? ፓርቲዋስ መቼና የት ከሕዝብ ተገናኝና "ዋና ተቃዋሚ ፓርቲ" ተባለ? የፓርቲው ፕሮግራምስ መቼ ነው ለኢትዮጵያ ሕዝብ የተሰራጨው ? ከተመሰረተስ ምን ያህል ጊዜ ሆነው? የመሳሰሉትን መጠየቅ አስፈላጊ ነው። "የቀንጅት ወራሽ" የሚለው አባባል የአራዳ ልጆች የሚመኙት ካልሆነ በቀር መዳብና ወርቅ፣ ዱባና ቅል ነገር ነው። እስቲ በትቂቱ እንመልከት።

አንድነት ፓርቲ ቀንጅትን ከድተው፣ ቀንጅትን ጥለው በሄዱ ሰዎች የ 1500 ሰው ፊርማ አሰባስበው በአዲስ ፓርቲነት ተመዝግበው በሰኔ 2000 ዓ.ም የተቋቋመ ነው። የዚህ ድርጅት መስራቾችና መሪዎች በቀንጅት ምስረታና በምርጫ 97 ውስጥ የነበራቸው ተሳትፎ፣ የፖለቲካ እድሜና ልምድ ከአንድ ወር እስከ ስምንት ወር በሚደርስ ጊዜ ውስጥ ሲሆን ያው ከአመራሮቹ መካከል ለሃያ ወራቶች ያህል በቃሊቲ መታሰራቸው የታወቀ ነገር ነው። አብዛኞቹ መሪዎችም ሆነ መስራቾቹ ከአዲስ አበባ

ወጥተው ሕዝብ አናግረውና አደራጅተው የማያውቁ ሲሆን፣ ይኸው አዲሱ ፓርቲ ከመሰረቱ በኋላ ጥቂት በገንዘብ የገዟቸው አደራጆች መኢአድ ከ4 እና 5 ዓመት በፊት ያደራጃቸው ቦታዎች የዘዋቸው በመሄድ ፎቶ ግራፍ ከመነሳት በቀር ያደራጁት ሕዝብ የለም:: አሁን በቅርቡ ጥቂት ጽህፈት ቤቶች ከፍተናል ካሉ ከሁለት ወራት ተኩል አይበልጥም: በአጭሩ የነብርቱካን አንድነት ፓርቲ የሚባለው በኢትዮጵያ ሕዝብ ዘንድ የማይታወቅ፣ መሰረት የሌለው፣ ደጋፊ የሌለው አዲስ ፓርቲ ነው:: በአዲስ አበባ አንድ የምስረታ አንድ ደግሞ ሕዝባዊ ስብሰባ ማድረጋቸው ተነግሮአል:: ታዲያ በየክፍለ ሀገሩ ሕዝብ ሳያደራጁ፣ ሕዝብ ደግሞ ድጋፉን ሳይሰጣቸው እንዴት ነው የኢትዮጵያን ሕዝብ የሚወክሉት? የኢትዮጵያን ሕዝብስ የትና መቼ ነው ያደራጁት? አሁን ለዚህ መልስ የላቸውም:: ገና እኮ ከተመሰረተ ስድስት ወር የሆነው ፓርቲ አመራሩ አንዴ ሶደሬ አንዴ ደብረዘይት እየሄደ "ሲሰጥን" ሕዝብን ማደራጃ ጊዜ አላገኙም ወገን:: አሁን አዲስ አበባ ውስጥ እንኳን "አንድነት ፓርቲ" ምን ያህል ደጋፊ አለው ቢባል አይን ፍጥጥ ይላል:: ደጋፊ አለን ቢሉ በውጭው አገር ያለው የከረንት አፌርስ፣ እንደ አሸን የፈላ ድኅረ ገጾችና በጥቂት ከተሞች ያሉ የተወሰኑ ደጋፊዎቻቸው ናቸው:: ፍየል ወዲህ ቅዝምዝም ወዲያ ይሏል ይህ ነው:: የኢትዮጵያ ሕዝብ አሜሪካና አውሮፓ አይደለ የሚኖረው:: ትግልና መደራጀት  በሳይበር ብቻ ቢሆን ኖሮ የሳይበር ሥልጣን የሳይበር መንግሥት ቢይዙ ይገባቸዋል እንላለን:: ዋናው ነገር እነ ብርቱካንም ሆኑ ፓርቲያቸው ኢትዮጵያ ውስጥና በኢትዮጵያ ሕዝብ ዘንድ መሰረት የሌላቸው የወያኔና የውጭ ኃይል መልዕክተኞች የወቅቱ የትግል ድራማ ተዋንያን ናቸው::

የሚገርመው መብራት ኃይል ሕዝባዊ ስብሰባ አደረግን ሲሉ አብዛኛው ደጋፊ የነስዬ አብርሃ ሰዎች መሆናቸው አንድ የሚጭር ነገር አለ:: አቶ ስዬ አብርሃ ንግግር ለማድረግ እነ ብርቱካን መድረክ ላይ ሲወጣ ሰዉ ከመቀመጫው ተነስቶ የነበረው ፉጨት ጭብጨባና ድጋፍ ለፓርቲው መሪ ለብርቱካንም አልተደረገ:: እነ አቶ ስዬ መንገዳቸውን እያመቻቹ፣ ምርጫው ሲቃረብ የሚመታውን አታሞ የሚናገር ንፋስ እየነፈሰ ነውና ንበዝ መመርመርና መጠንቀቁ ካሁኑ ነው:: መቼም የልደቱን ድራማና የሰራውን ስራ የሚዘነጋ ያለ አይመስለንም:: የልደቱ ዝና በየአጋጣሚው እየተጋነነ ሄዶ ማንዴላ ሲባል የበቃበት ምክንያት ልክ ዛሬ እየተካሄደ ካለው ስራ ጋር ምንም ልዩነት የለውም::

ኸረ ለመሆኑ ብርቱካን ለኛ ታስራ በዚያው ዕለትና በማግስቱም እነ ቢቢሲ በሰፊው የዘገቡት፣ እነ VOA ሔና ጀርመን ሬዲዮ ጣቢያ በየቀኑ የዜና ሽፋን የሰጡት፣ ለኛ ታስራ ማከለኛ የአሜሪካ ኤምባሲ "የብርቱካን መታሰር በጣም እንዳሳሰበው" መግለጫ ሲሰጥ፣ ሳምንት ሳይሞላ አምነስቲ ኢንተርናሺናል "የህሊና እስረኛ" ሲላት፣ ከታሰረች ሁለት ሳምንት ሳይሞላት፣ የአውሮፓ ዩኒየን በፓርላማው የብርቱካንን መታሰር አስመልክቶ በውሳኔ እንድትፈታ ሲጠይቅ፣ የእንግሊዝ ኤምባሲ በብርቱካን መታሰር ስጋቱን ሲገልጽ፣ የኮንግረስና የሴኔት አባሎች እንድትፈታ በደብዳቤ ሲጠይቁ፣ በአገር ቤትም የነስዬ አበርሃ መድረክ ብርቱካን ትፈታ ሲል መግለጫ ሲያወጣ፣ የትግራይ ተወላጆችም ብርቱካን ትፈታ የሚል መግለጫ ሲያወጣ ኸረ ለመሆኑ ብርቱካን ምን ሰርታና በምን ምክንያት ነው ይኸ ሁሉ ርብርቦሽ? ምነው እነ ፕሮፌሰር አሥራት አምስት ዓመት ያህል ታስረው ሲሰቃዩ ስንቶቹና እነማን ነበሩ በአጭር ጊዜ ውስጥ መልስ የሰጡት? ድፍን የኢትዮጵያ ሕዝብ ሲገደል፣ ሲጨፈጨፍ፣ ሲታሰር ምነው ይህን ያህል ዓመት መልስ ሳይሰጡ መስስን ሲደግፉ ኖሩ?  ታዲያ ብርቱካን ምን ሰርታና በምን ምክንያት ነው የተለየ ትኩረት የተሰጣት? የትግራይ ተወላጆችስ ዛሬ ምን ታያቸው? አሁን ብርቱካን ወደ ቃሊቲ ስትሄድ በቅንጅት ውስጥ የአንድ ወር ያህል እድሜም አልነበራት:: ዝናዋ ግን ከሌሎች እስረኞች የበለጠ ገኗል:: ከቃሊቲ ከወጣች በኋላም የሞቱላትን የሰፈርዋን ሰዎች እንኳን ሳታጽናና አሜሪካ የመጣች መሆኑን አንዘነጋውም:: ዛሬ የትግራይ ተወላጆች ማህበርና አረና ትግራይ ድጋፋቸውን የሰገሷት ሚኒሶታ ላይ በቅንጅት ስም የትግራይን ሕዝብ ይቅርታ ስለጠየቀች ይሆን? በኮንግረስ ፊት 100 እስረኛ ብቻ ነው ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ስላለች ይሆን ዛሬ የኮንግረስ አባላት የሚጮሁላት? ወያኔ ጠላታችን አይደለም፣ ከወያኔ ጋር ለመስራት ቀዳዳ አለ፣ ከወያኔ ጋር ሳንፋታ ተጋብተናል ማስተዋስ ለምን ነበር? መኢአድ የደራጃቸውን ሰዎች እየሄደች ኑ ወደ እኛ ግቡ እያለች በገንዘብ ማባባሏ ይሆን ሕዝብ አደራጀን ያለችው? ታዲያ በየትኛው ተግባርዋ ነው ብርቱካን ዝነኛ የሆነችበት? "የተማረች፣ ሴት፣ ኦሮሞ፣ ወጣት" የሚለው ክራይቴርያ ይሆን? ስዬ አብርሃን በዋስ ስለፈታች ይሆን ዝነኛ የሆነችው? ወይስ መታሰርዋ ይሆን? አሁን የሚል ካለ በጣም ተሳስቷል::  ብዙ ሺ

ኢትዮጵያኖች እኮ የታሰረ፣ የተደበደቡ፣ አካለ ጎደሎ የሆኑ አሉ:: · ጎድ አኮ ነው በየፓልቶኩም የወያኔ ቀንደኛ ደጋፊዎች የሆኑ ግለሰቦች "ብርቱካን ሚዴቅሳ ወፈያችን ነች፣ ጠቅላይ ሚኒስትራችን ነች እንድትፈታ ሰልፍ መውጣት አለብን" እያሉ ሲቀሰቅሱ በትዝትብት አዳምጠናል:: እነ ሰዬ አብርሃ ብርቱካንን ለጠቅላይ ሚኒስትርነት አጭተውልን ይሆን በ2010 ምርጫ? እግዜር ይወቀው:: ለነገሩ ብርቱካን የሕዝብ ተመራጭም አልነበረች:: የብርሃኑ ነጋ ምርጫ እንጂ:: ዛሬም ቢሆን የ6 ወር እድሜ ያስቆጠረው ፓርቲዋ የኢትዮጵያ ሕዝብ ምን እንደሚለው አለስማንምና የፓርቲዋ መሪ እንጂ የኢትዮጵያ ሕዝብ መሪ ለመሆን ብቃቱም፣ ልምዱም፣ ችሎታውም፣ የሕዝብ ድጋፍም የላት:: በዜግነትዋ በፖለቲካ እምነትዋ መታሰርዋን ማንም አይደግፍም:: መቃወምም አለብን ሆኖም ግን አደገኛ የሆነውን የልደቱን ማንዴላ አይነት ካብ ለብርቱካን መስጠት አደጋው ካሁኑ ሊታሰብበት ይገባል::

አገር ቤትማ ሕዝቡ ስለ ብርቱካን መታሰር ምን ይላል ለማለት ደውዬ የማውቃቸውን ሰዎች በየቦታው ብጠይቅ ማንም ሰው ቦታ የማይሰጠው ነገር መሆኑን ከብዙ ሰዎች ስሰማ ወይ ጉድ አልኩ:: ሕዝብ እኮ በየቀኑ እየታሰረ፣ እየተደበደበ፣ እየተገደለ፣ ከስራ እየተባረረ፣ እንደ ብርቱካን ፈልጎ ሳይሆን የሚበላው አጥቶ ጦሙን ውሎ ጦሙን የሚያድር መሆኑን ነገሩኝ:: 80 ሚሊዮን ሕዝብ እኮ እስር ቤት ውስጥ እያለ እኛን ከድታ ትግሉም ከድታ ለሄደች ሰው ሕዝቡ ደንታም አይሰጠው አሉኝ:: የታሰረች ዕለት ሲቪል የለበሱ 10 ሰዎች ከመኪና ወርደው እርሷን እያዳፉ ፕሮፌሰሩን በሰደፍ ፊኛቸውን መመታታቸውን በዜና ሰምተን አዝነናል:: አንዱ አዲስ አበቤ ሲቪል ለባሾቹ ጠመንጃ አይሸከሙም የወታደር ዩኒፎርም ካልለበሱ ነጭ ለባሾች ሽጉጥ ብቻ ነው የሚይዙት ቢለኝ ግራ ገባኝ ምክንያቱም ፕሮፌሰሩ "በሰደፍ ፊኛዬ ላይ መቱኝኝ ሲሉ በጠመንጃ ሰደፍ መስሎኝ ነበር:: ያዮ ቢነግረን መልካም ነበር::

በመግቢያው ላይ የዛሬ ሶስት ዓመት በፊት የነበረውና የሰሞኑ ትግል ልዩነትን የጠቀስቁት ያለምክንያት አይደለም:: ሰሞኑን የሚደረገው ረጫና ግርግር፡ እውነተኛ ታጋዮችን ለመሸፈን የሚደረግ ከፍተኛ ደባና ሴራ ሲሆን፣ ትግሉ በቀጥታ ከወያኔ ጋር እንዳይሆን በመካከሉ የገቡ የፖለቲካ ደንቃሮች መሰናክል እየሆኑ ታጋዩን ክፍል እንደ ጋሬጣ እየቀደዱ ለመጣል የሚደረግ ውንብድና ነው:: ብርቱካንን ከሰው በላይም እንደ መላዕክት እንደ አማልክት እንድትመለክ በየጊዜው የሚጽፉ የምሁር ደንቆሮዎች ፕሮፌሰር እከሌ እንዲህ ብሏል ዶክተር አከሌ ስለ ብርቱካንን እንዲህ አለ እየተባለ "አባኪያ" በሚል ስም አንዱ ባለጉድሮ የፖለቲካ ደንቃራ ሲጽፍ አይቼ ግብዝነቱ አሳዘነኝ:: የውሸት ጀግና የሚፈጥረልን የፖለቲካ ደንቃሮችና ምሁር ተብዬዎችን ታገሱ፣ ታቀቡ ማለት አስፈላጊ ነው::

ትግላችን እውነተኛ ዲሞክራሲን ለማምጣት፣ ከዘረኝነትና ከጎሳ ፖለቲካ የጸዳ፣ በሕዝብ ፈቃድና ምርጫ የተመረጠ መንግስት ለመመስረት፣ ሰላም እድገትና ብልጽግና ለሀገራችን ለማምጣት እንጂ፤ ትላንት አንቀጽ 39ን አጽድቀው አገር ሲገነጥሉ፣ ሕዝብ ሲጨፈጭፉና ሲያጨፋጭፉ፣ አገር ሲመዘብሩና ሲያጠፉ የነበሩትን ኃይሎች ወንጀላቸውን ደብቀን ለውጥ የተደረገ ለማስመሰል እነ መለስና ካምፓኒውን በሰላም የመኖር ዋስትናቸው ተሰጥቷቸው የዘረፉትን ሀብት ሲበሉ ሌላው መለስ ደግሞ ተቀምጦ አገር እንዲያጠፉ በሚደረገው ደባ ውስጥ ባለማወቅ ተባባሪና ደጋፊ እንዳንሆን መጠንቀቅ አለብን:: የታሰበውም የሚሰራውም ድራማ ሁሉ ተነቅቷልና በጽኑ እንዋጋዋለን::

ትላንት በዋሽንግተን ዲሲ መቶ ሺ ሰው ይወጣል ሲሉኝ እንደው ጉድ አያለሁ ብዬ ከስራ ፈቃድ ወስጄ ሄጄ ነበር እንዲያውም ትራፊክ እንዳያዘገየኝ ፈርቼና ቦታም አላገኝ የሚለው ስጋቴ አንድ ሰዓት ቀደም እንድል አድርጎኝ ነበር:: ያተረፍኩት በብርድ መጠበስ ነበር:: ለመሆኑ መቶ ሺ ስንት እንደሆን አደራጆቹ አያውቁም ማለት ነው? አንድ ሰዓት ያህል ጠብቄ መቶ ሰውም አልነበር:: የዛሬ ሶስት ዓመት በፊት በ 10 ሺህ እና 20 ሺህ ያህል ሰላማዊ ሰልፈኛ እንዳልወጣን ሁሉ ዛሬ "ወይ ዲሲ" አልኩኝ:: ስለ ተዋንያኑ "አስተባባሪዎች" ሌላ ጊዜ እመለሳለሁ::

ጥር 7 ቀን 2001 ዓ.ም
ዋሽንግተን ዲሲ